መልእክት አራት

## የሰሎሞን ድንቅ መንግሥት
## በሺሁ ዓመት የሚኖረውን የክርስቶስን መንግሥት በምሳሌ ማሳየቱ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- 1 ነገ. 10፡1-24፤
መዝ. 72፡1-8፣ 11፣ 17-19፤ ራእ. 11፡5፤ 20፡4፣ 6

**I. በእግዚአብሔር የበለጠገ በረከት ሥር ካለው ብልጽግናው ጋር፣ የሰሎሞን ድንቅ መንግሥት በሺሁ ዓመት የሚኖረው የክርስቶስ መንግሥት ምሳሌ ነው—1 ነገ. 4፡20—5፡18፡-**

ሀ. በ 1ኛ ነገሥት ያሉት ምዕራፍ 9 እና 10 በአሕዛብ መካከል የሰሎሞንን ክብር ከፍተኛ ጫፍ ያሳያሉ።

ለ. ሰሎሞን በመንግሥቱ ግርማ በእስራኤል መንግሥት ከብሮ ነበር፤ ይህ በሺሁ ዓመት የክርስቶስ ቅድመ-ማሳያ ነው—ቁ. 1-24።

**II. ክርስቶስ በሁለተኛ መምጣቱ ርስት ተደርጎ የተሰጠውን ምድር ለራሱ ያደርጋል፣ የእግዚአብሔርንም መንግሥት በምድር ሁሉ ይመሠርታል፣ ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር በምድር ላይ ያለውን መብት ይመልሳል—መዝ. 24፡1፡-**

ሀ. መዝሙር 24፡7-10 በእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት ውስጥ እንደሚመጣው ንጉሥ አሸናፊውን ክርስቶስ ይገልጣል።

ለ. ያሕዌ ኢየሱስ ነው፣ ኢየሱስ ደግሞ በውጊያ ብርቱ እና አሸናፊ የሆነው ሥጋ የለበሰው፣ የተሰቀለው እና ከሞት የተነሣው ሦስታንዱ አምላክ ነው—ራእ. 5፡5።

ሐ. እርሱ ምድርን መንግሥቱ አድርጎ ለመውረስ በትንሣኤ ከድል ነሺዎቹ ጋር ተመልሶ የሚመጣው ነው—ዳን. 2፡34-35፤ 7፡13-14፤ ኢዮኤል 3፡11፤ ራእ. 11፡15፤ 19፡13-14።

**III. መዝሙር 72 በሚገዛው ሰሎሞን የተመሰለው የሚገዛውን ክርስቶስ የሚመለከት ነው፡-**

ሀ. መዝሙር 72 እንደሚገዛው ማንነት የክርስቶስ ምሳሌ የሆነውን ንጉሥ ሰሎሞንን የሚመለከት መዝሙር ነው—ማቴ. 12፡42፡-

1. ሰሎሞን የዳዊትን ዙፋን እና መንግሥት እንደሚወርሰው እንደ ዳዊት ልጅ የክርስቶስ ምሳሌ ነው—1፡1፤ 2 ሳሙ. 7፡12-13፤ ሉቃ. 1፡32-33።
2. በዳዊት መከራዎች እንደተመሰለው በምድር ላይ መከራ ከተቀበለበት ሕይወቱ በኋላ ክርስቶስ፣ በሰሎሞን ወደተመሰለበት አሁን እንደ ንጉሥ እየገዛ ወዳለበት ወደ ሰማያት ዐረገ—1 ቆሮ. 15፡25፤ ራእ. 17፡14።

ለ. በመዝሙር 72 ርዕስ እና በመጀመሪያው ቁጥር እንደተመለከተው የሚገዛው ክርስቶስ በስኬታማው እና በማበቡ ጊዜ (1 ነገ. 9—10) በሚገዛው ሰሎሞን (ማቴ. 1፡1፤ 22፡42) ተመስሏል፡-

1. መዝሙር 72 ነገሥታት ሁሉ የሚሰግዱለትን እና አሕዛብ ሁሉ የሚያገለግሉትን በምድር ላይ የሚገዛውን ክርስቶስ ይገልጣል—ቁ. 1-8፣ 11።
2. መዝሙር 72 ጌታ ምድርን በሙሉ መመለሱ፣ የራሱ ማድረጉ እና በምድር ሁሉ ላይ መግዛቱ ምን እንደሚመስል የሚያሳይ የከበረ ስዕል ነው—ቁ. 17-19።
3. በሰሎሞን የተመሰለው የክርስቶስ መግዛት በመታደስ ዘመን በሺሁ ዓመት መንግሥት ይሆናል—ራእ. 20፡4፣ 6፤ ማቴ. 19፡28።

**IV. "የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል"—ራእ. 11፡15፡-**

ሀ. የክርስቶስ መንግሥት ሺሁ ዓመት ነው፤ በተጨማሪም የእግዚአብሔር መንግሥት ነው—20፡4፣ 6፤ ማቴ. 16፡28፤ 13፡41፣ 43።

ለ. በመንግሥቱ ገጽታ እንደ የክርስቶስ እና የእግዚአብሔር መንግሥት፣ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ይገዛል፤ ክርስቶስ እንደ እግዚአብሔር ይነግሣል ማለትም ጭምር እንችላለን—ራእ. 11፡15።

ሐ. ክርስቶስ ፍርዱን በአሕዛብ ላይ ካስፈጸመ በኋላ ተመልሶ ሲመጣ የዓለም መንግሥት የክርስቶስ መንግሥት ትሆናለች—ዳን. 7፡13-14፤ 2፡44-45።

መ. በራእይ 11፡15 የጌታ ከዘላለም እስከ ዘላለም መንገሥ በሺሁ ዓመት መንግሥት እና ለዘላለም በአዲሱ ሰማይ እና በአዲሱ ምድር የጌታ መንገሥ ነው—ራእ. 22፡5።

ሠ. ሁሉም ድል ነሺዎች ለአንድ ሺህ ዓመታት ከክርስቶስ ጋር አብረው ይነግሣሉ፣ የዳኑ ሁሉ በዘላለም ውስጥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ—20፡4፣ 6፤ 22፡5።

**V. ጌታ ኢየሱስ አማኞችን፣ አይሁድን እና አሕዛብን ከፈረደ በኋላ፣ ሺህ ዓመቱን—ለአንድ ሺህ ዓመታት በምድር ላይ የክርስቶስን እና የእግዚአብሔርን *መንግሥት*—*ያመጣል*—20፡4፣ 6፡-**

ሀ. ሺሁ ዓመት የሚያመለክተው ክርስቶስ ዓለምን ለመግዛት ዳግም ከመጣ በኋላ ያለውን እና ከአዲሱ ሰማይ እና ከአዲሱ ምድር በፊት ያለውን ጊዜ ነው።

ለ. በሺሁ ዓመት ጊዜ አሕዛብ ሁሉ ወደ ክርስቶስ ይመጣሉ—ዘካ. 14፡16።

ሐ. በብሉይ ኪዳን የሺህ ዓመቱን መንግሥት በተመለከተ ብዙ ጥቅሶች አሉ—መዝ. 2፡6፣ 8-9፤ ኢሳ. 2፡2-5፤ 11፡1-10፤ 65፡20-25፤ ዘካ. 8፡20-23፤ 14፡16-21።

መ. በሐዋርያት ሥራ 3፡21 *ነገር ሁሉ የሚታደስበት ዘመን* የሺህ ዓመቱን መንግሥት ያመለክታል፡-

1. ይህ መታደስ ሰው ላይ ብቻ ሳይሆን መላው አጽናፍ-ዓለም—ሰማያት፣ ምድር፣ እንስሳት እና ዛፎች—ላይ ተጽእኖ ያመጣል።
2. በሰው ውድቀት አማካይነት የተረገመ ነገር ሁሉ ይታደሳል—ኢሳ. 11፡6፤ 30፡26።

ሠ. ሺሁን ዓመት እግዚአብሔር እንደ የዝግጅት ዘመን ይጠቀምበታል፡-

1. በቤተ ክርስቲያን ዘመን ፍጹማን ያልሆኑትን ቅዱሳን ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት ወደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለመግባት ብቁ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ፍጹማን ያደርጋቸዋል።
2. በሺህ ዓመቱ ጊዜ የታደሱት አሕዛብ በአዲሱ ምድር ያሉ ሕዝብ እንዲሆኑ እግዚአብሔር ያጠራቸዋል።

ረ. በእግዚአብሔር ልጅ በክርስቶስ የሚያምኑ አማኞች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ዳግም ተወልደዋል፣ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ፣ ዛሬ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እየኖሩ ቢሆንም፣ በሺሁ ዓመት የሚሳተፉት ግን ሁሉም አማኞች ሳይሆኑ ድል የነሡት ብቻ ናቸው—ዮሐ. 3፡5፣ 15-16፤ ሮሜ 14፡17፤ ራእ. 12፡10-11፤ 2፡26-27፤ 3፡21።

**VI. በማቴዎስ 16፡28—17፡5 የሚታየው ነገር በሺሁ ዓመት የሚኖረው ትንሹ የመንግሥተ ሰማያት መገለጥ ነው፡-**

ሀ. የዚህ የትንሹ መንግሥተ ሰማያት ማዕከል የከበረው ኢየሱስ ነው፣ ከእርሱም ጋር የብሉይ ኪዳን ድል ነሺዎችን የሚወክሉት ሙሴ እና ኤልያስ እና የአዲስ ኪዳን ድል ነሺዎችን የሚወክሉት ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ እና ዮሐንስ አሉ—ቁ. 1-3።

ለ. በተራራው ላይ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ እና ዮሐንስ የሚመጣው የመንግሥቱ መገለጥ ቅድመ-ቅምሻ ነበራቸው—16፡28—17፡3።

ሐ. ጌታ ኢየሱስ መለወጡ ማለት ስብዕናው በመለኮትነቱ ተሞልቶ እና ተሰርጎ ነበር ማለት ነው፤ ይህ መለወጥ መክበሩ ነበር—ቁ. 2፡-

1. የጌታ ኢየሱስ መለወጥ፣ ማብራት በመንግሥቱ መምጣቱ ነበር፤ መለወጡ ባለበት፣ የመንግሥቱ መምጣት አለ—ማር. 9፡1-4፤ ሉቃ. 9፡27-31።
2. የጌታ ኢየሱስ መለወጥ እርሱ የሆነው ነገር እውን መሆን ነበር።
3. መንግሥቱ የጌታ ኢየሱስ እውነታ ማብራት ነው፤ በማብራቱ ሥር መሆን በመንግሥቱ ውስጥ መሆን ነው—ራእ. 22፡4-5።
4. በሺሁ ዓመት ድል ነሺዎቹ አማኞች በመንግሥቱ ብሩህ ክብር ውስጥ ከክርስቶስ ጋር ይሆናሉ፡- "በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ"—ማቴ. 13፡43 እና የግርጌ ማስታወሻዎች 1 እና 2።

© 2022 Living Stream Ministry